የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 40
ADDIS ABABA, 24th April, 2015


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፯/፪ሺ፯ ዓ.ም

የምስራቅ አፍሪካ የተጠንቀቅ ሃይልን ለማቋቋም የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……………………ገጽ ፰ሺ፪፻፴፭


## አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፯/፪ሺ፯ ዓ.ም

### የምስራቅ አፍሪካ የተጠንቀቅ ሃይልን ለማቋቋም የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የምስራቅ አፍሪካ የተጠንቀቅ ሃይልን ለማቋቋም የተደረገው ስምምነት ሰኔ ፲፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም በማላቦ የምስራቅ አፍሪካ ርዕሳነ ብሄሮችና መንግስታት በሶስተኛው አስቸኳይ የመሪዎች ስብሰባ ላይ የፀደቀና በአገራችን የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**CONTENTS**


Proclamation No.887/2015

The Eastern Africa Standby Force Establishment Agreement Ratification Proclamation…page 8235


## PROCLAMATION NO. 887/2015

### A PROCLAMATION TO RATIY THE AGREEMENT ON THE ESTABLISHMENT OF THE EASTERN AFRICA STANDBY FORCE

WHERE AS, the agreement on the Establishment of the Eastern Africa Standby Force was adopted on the 26th of June 2014 at the 3rd extra ordinary Meeting of the Assembly of Heads of State and Government of the Eastern Africa Region held in Malabo;

WHEREAS, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified this Agreement at its ordinary session held on the 2nd day of April , 2015;

NOW THEREFORE; in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution ,it is here by proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የምስራቅ አፍሪካ የተጠንቀቅ ሃይልን ለማቋቋም የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፯/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

ምስራቅ አፍሪካ ርዕሳነ ብሄሮችና መንግስታት ሰኔ ፲፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም በማላቦ ባካሄዱት ሶስተኛው አስቸኳይ የመሪዎች ስብሰባ የተፈረመው የምስራቅ አፍሪካ የተጠንቀቅ ሃይልን ለማቋቋም የተደረገው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫.<u>የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ስልጣን</u>**

የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ይህን ስምምነት እንዲያስፈፅም በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "The Eastern Africa Standby Force Establishment Agreement Ratification Proclamation No.887/2015."

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Agreement on the Establishment of Eastern Africa Standby Force adopted on the 26th of June 2014 at the 3rd extra ordinary Meeting of the Assembly of Heads State and Government of the Eastern Africa Region held in Malabo, is hereby ratified.

**3. <u>Responsibility of the Ministry of National Defense</u>**

The Ministry of National Defense is hereby empowered to undertake all acts necessary to implement this agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 24th day of April, 2015.

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**